# ራቁቱን የቀረው የሻዕብያ አመራር

እንደ አበደ ውሻ ካገኘው ጋር የሚናከሰው የኤርትራ መንግስት ከቀን ወደ ቀን በሚሰራቸው ስራዎች የአለም ህዝቦች ጠላት መሆኑን በፈጣን ሁኔታ በማረጋገጥ ላይ ያገኛል::

ይህ መንግስት ሲያሰኘው ሀቀኛ፣ ለእውነት የቆመና ሌሎችን ለመረዳት የተፈጠርኩ ነኝ በማለት የሌሎችን ሰላም ይነሳል:: ሲያሰኘው ደግሞ ያገኘውን መሪ፣ አገር እንዲሁም አለም አቀፍ ድርጂቶችን ይሳደባል ፣ ይዘረጥጣል፣ ሲያሰኘውም አዳዲስ ስሞችን በመስጠት ይፈረጃል:: የአፍሪክ ህብረት ድርጅትና መሪዎች የዘወትር የአፉ ማሟሻና መሳለቂያ ናቸው:: «ዝንጀሮ የራሷን ጠባሳ ሳታይ በባልጀራዋ ጠባሳ ትስቃለች» እንደሚባለው ሌሎች አገሮች የሚያደርጉትን የዕድገትና የማህበራዊ እንቅስቃሴ ሲያጣጥልና ሲያንቋሽሽ ይታያል:: ባለፉት 16 ዓመታት በኤርትራ ምድር ትርጉም ያለው የዴሞክራሲያዊ አሰራርና ስርዓት ሳይገነባ ሌሎች አገሮች እነዚህን ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ለመገንባት በሚያደርጉት ጥረት ያሾፋል:: ሲያሰኘውም ለማደናቀፍ ይሯሯጣል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሽብረተኞችን በመደገፍ፣ በማስታጠቅ የአጎራባች አገሮችን ሰላም ከማወክ አልፎ በቀጥታ ወደ ሽብር ተግባር



መጋቢት/1999 March/2007

ሰሞነኛ

በመግባት ላይ ይገኛል:: ከዚህ አባበላችን አንፃር በተደጋጋሚ የሻዕብያ ሴራ ሰለባ በመሆን የምትገኘው አገራችን ኢትዮጵያ ናት::

የኢትዮጵያ መንግስትና ኢህአዴግ የኤርትራ ህዝብ ዴሞክራሲአዊና ሰላማዊ በሆነ መልክ ራሱን እንዲችል ያልተቆጠበ ጥረት ቢያደርጉም፣ የሻዕብያ አመራር በእብሪት በመነሳሳት ያጎረሰወን ዕጅ በመንከስ ድንበራችን በመውረር በወንድማማች ህዝቦች መካከል ደም በማቃባት ጠላትነትን ለማቀጣጠል ሞከረ:: ዳሩ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ አኩሪ የመስስዋዕትነት ታሪክ በመስራት ሻዕብያን በወቅቱ ማሳፈር ተችሏል:: ከዚያ ወዲህ በዕየለቱ እየአሰረገ በሚያስገባው ሽፍታና አሸባሪ አማካኝነት ሰላምና ልማታችንን ለመፈታተን ቢጥርም እንደ አመጣጡ በመመከት ቀዳዳ እንዳያገኝ ለማድረግ ተችሏል:: የተለያዩ አሸባሪ አካላትን «ነፃ አውጪ» በሚል ስም እየአደራጀ፣ እየአሰለጠነና እየአስታጠቀ የህዝባችንን በሰላም ውሎ መግባት ችግር ላይ ሲጥል ይታያል::

በተለይም በሱማሌ በኩል የተባበሩት የእስልምና ጉባዔ አባላትን ታዛ በማድረግ አገራችንን ወደ ማያባራ ጦርነት ለመክተት የወጠነው ሤራ ፈጣንና አመርቂ በሆነ መልክ አከርካሪውን በመምትት ማፈራረስ በመቻሉ ሌላ የዕፍረት ሸማ እንዲከናነብ አድርጓል:: ይህ ተግባርም የአለም ህዝብ የሻዕብያን እኩይ ዓላማ በግልፅ እንዲያወቅና እንዲገነዘብ አድርጓል::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

## *ሰሞነኛ*

ከአንዱ የቀውስ አዙሪት ወደ ሌላው የቀውስ አዙሪት የሚጣደፈው ሻዕብያ በአፍሪካ በአጠቃላይና በኢትዮጵያ በተናጠል የሚያውተበትበው የተንኮልና የሽብር መረብን ተግባራዊ ለማድረግ የሰለጠኑ የፈንጂ ባለሞያዎችን ቢያሰማራም ከኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ዓይን መሰወር ባለመቻሉ ሲጋልጠጥና ሌላ እፍረትን በአለም ህዝብ ፊት ሊከናነብ ችሏል::

እብሪተኞች የያዛቸው የትዕቢት እብደት ሳያጠፋቸው መቆም አይችልምና ያለፉት የተለያዩ የቅሌትና ሽብር ሙከራዎች ያከናነቡት የውርደትና የሀፍረት ደመና ሳይገልጥ በአፋር ክልል ወኪሎቹን በመላክ በአገር ጎብኚ የውጭ ዜጎችና እነሱን ሲረዱ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን በማስጠለፍ ሌላ የሽብር ተውኔት ለመስራት በመደፋደፍ ላይ ይገኛል::

የኢትዮጵያ መንግስትና ሰላም ወዳድ የአለም አቀፍ ወገኖች ባደረጉት ጥረት የውጭ ዜጎቹ የተለቀቁ ቢሆንም፣ በዕለታዊ የአስጎብኝነት ተግባራት ተሰማርተው የነበሩ 8ቱ ኢትዮጵያውያን ግን እስከ አሁን አልተለቀቁም:: ወገኖቻችንን ለማስለቀቅ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝብና የአለም አቀፍ ሰላም ወዳዶች የሚያደርጉት ጥረት የቀጠለ ቢሆንም፣ በሽብር ተግባር የተሰማራው ሻዕብያ ከዚህ ተግባሩ የሚታቀብበት ባህሪ እንደሌለው ተደጋጋሚ ተግባራቱ መስክረዋል::

**Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia**
**3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010**
**Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org**
**www.ethioconsulate-la.org**

*መጋቢት/1999 March/2007*

## *ሰሞነኛ*

የኢትዮጵያ መንግስት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መግለጫ አማካኝነት የታገቱ ወገኖቻችን እንዲለቀቁና ሻዕብያ ከዚህ መሰል አሸባሪ ተግባራት እንዲታቀብ ጠንካራ መልእክት አስተላልፏል::

የኤርትራ ህዝብም ከጀርባው ላይ ተፈናጥጦ፣ የዴሞክራሲ መብቱን በመገደብ፣ያሻውን በመፍለጥ፣ በመቁረጥ ላይ የሚገኘውን ሻዕብያን ከእንግዲህ በቃህ ሊለው ይገባል:: የዚህን ዕብሪተኛ መንግስት ግፍና የጫነበትን መከራ በተባበረ ክንዱ ማስወገድ አለበት: :ሻዕብያ ያመጣለት ነፃነት ሳይሆን ባርነት፣ ብልፅግና ሳይሆን ድህነትን፣ መቻቻልን ሳይሆን መናቆርን፣ በማንነት መኩራት ሳይሆን መሸማቀቅን በመሆኑ ሻዕብያ በማንኛውም መለኪያ የኤርትራ ህዝብ ዋነኛ ጠላት ነው:: በመሆኑም ለዕብሪተኛና ለፀረ ህዝብ የሚገባውን ቅጣት በመስጠት የኤርትራ ህዝብ የአጎራባች ህዝቦች ፣ የአፍሪካ ጭቁን ህዝቦች ፣ የአለም ሰላም ወዳድ ህዝቦች ወገን መሆኑን ማረጋገጥ አለበት:: የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ለዴሞክራሲ ፣ለሰላምና ለፍትህ የሚደረገውን ትግል በፅኑ የሚደግፍና የሚያበረታታ መሆኑ ከዚህ ቀደም ያደረጋቸው ዴሞክራሲአዊ ድጋፎች በቂ ምስክር ናቸው::

በአጠቃላይ የኤርትራ ህዝብ የነፃነት ጎኅ ይቀድለት ዘንድ እምቢ ለዕብረኛ በማለት በሻዕብያ መቃብር ላይ አዲስ የሰላምና የፍትህ ሰንደቅ ማውለብለብ አለበት::

**Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia**
**3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010**
**Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org**
**www.ethioconsulate-la.org**